"በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን"

እንኳን በሰላም መጣችሁ

መጋቢት 28 2017 ዓ.ም ለሚኖረን ጉዞ የተዘጋጁ መዝሙራት

፩/1.እግዚአብሔር ይመስገን(ቁ.2)

እግዚአብሔር ይመስገን ይህችን ቀን ቀድሶ ለሰጠን/2×/
ከያለንበት <u>ሰብስቦ</u>(2×) ለዚህ ያደረሰን/4×/

፪/2.ቸርነቱ

ቸርነቱ በእኛ ላይ ስለበዛ/2×/
ይክበር ይመስገን መድኃኔዓለም የዓለም ቤዛ/4×/

፫/3.መድኃኔዓለም አዳነን

መድኃኔዓለም አዳነን በማይሻር ቃሉ/2×/
<u>ደስይበለን</u>(2×) <u>እልል በሉ</u>(2×) አዳነን በማይሻር ቃሉ/2×/
እናታችን ቅድስት የዓለም ምሕረት/2×/
<u>እንስገድላት</u>(2×) <u>እንስገድ</u>(2×) በእውነት የአምላክ እናት/2×/
ተዋህዶ ሃይማኖት እንከን የሌላት/2×/
<u>እንከተላት</u>(2×) <u>እስከ ሞት</u>(2×) በእውነት ያለ ፍርሃት/2×/
ጻድቃን ሰማዕታት ወሐዋርያት/2×/
<u>ያማልዱናል</u>(2×) <u>መላእክት</u>(2×) በእውነት በላይኛው **ቤት/2×/**

፬/4.ተወዳጅ ልጅሽን

ተወዳጅ ልጅሽን ህማሙን ስታይ
ማሰብ ይሳነኛል የአንቺን ስቃይ
በሾህ አክሊል ጉንጉን የቆሰለ ራሱ
በብዙ ግርፍት የታመመ አካሉ

በዕፅ መስቀሉ የወረደ ደሙ
የቀራንዮ ግፍ እጅግ ማስገረሙ
ደጉ ልጅሽ ታስሮ የፍጥኝ ሲሰቃይ
ተሰክቶ ቀረ አይንሽ ወደ ሰማይ

ስለመሰቀሉ አይሁድ ሲደሰቱ
ሲስቁ ሲያሾፍ ቁማር ሲጫወቱ
ሲዘባበቱበት አይንሽ በማየቱ
ህሊናሽ ተገርፏል በሀዘን በብርቱ

ብላቴናይቱ የዳዊት ልጅ ማርያም
ስለደረሰብሽ ቢነገር አያልቅም
ተጠማው ሲላቸው መፃፃ አስጎነጨት
መርገም አስውግዶ ቢሰጣቸው ህይወት

ለመጠጡ እንዲሆን መፃፃ ከሐሞት
ሰፍነግን ጨምረው በዘንግ አስጎነጨት
ዳዊት በትንቢቱ እንደተነበየው
በምግቤ መራራን ጨመሩ እንዳለው

ይህ ሁሉ ሲሆን ድንግል ተመልከታ
መፅናናት ተሳናት በሐዘን ተነክታ
ኤሎሄ ኤሎሄ ጌታ ባለ ጊዜ
እጅግ ኃያል ነበር የማርያም ትካዜ

፭/5.ሳይገባኝ

ሳይገባኝ አምላክ ሳይገባኝ
ሳይገባኝ ጌታ ሳይገባኝ
ለዚህ ያደረስከኝ እኔ ማነኝ?
ለዚህ ያደረስከን እኛ መነን?
ምን ያላረክልኝ አለ ጌታ ለእኔ
ምንም ባሳዝንህ በምግባሬ
ኃጢአቴን ተመልክተህ ቸል ያላልከኝ
በህይወቴ ብዙ ነገር ሰራህልኝ
ውለታህ ብዙ ነው ያንተ ወሰን የለው
ተናግሬ እኔ አልጨርሰው
ውድቀቴንም ድክመቴንም እኔ አውቃለሁ
የጠበቀኝ ቸርነትህ ምሕረትህ ነው
ለማይነገረው ፍቅርህ ግሩም ስራ
ልጆችህን የምትጠብቅ ከመከራ
ምን እንመልሳለን ላንተ ለአምላካችን
ከመዋረድ አድነኸን ላከበርከን

፮/6.አልፋና ኦሜጋ

አልፋና ኦሜጋ ፈጣሪ የሆንክ
በከሀዲዎች እጅ ተይዘህ ቀረብክ/2×/
ተገፋህ ተደፋህ በጥፊ ተመታህ
እየደበደቡህ ክርስቶስ ሆይ አሉህ
ጽድቅን ስለሰራህ በወንጀል ከሰሱህ
ለአዳም ቤዛ ብለህ ብዙ ተንገላታህ
ቅዱሳን እጆችህ የፊጥኝ ታሰረው
እንደ በግ ጎተቱህ ልትምራቸው
የትም ቦታ ያለህ ሁሉን የምታውቅ

ፊትህን ሸፈኑህ ለመመጻደቅ
በዚያ በአደባባይ በጲላጦስ ዘንድ
አሳልፈው ሰጡህ አጋልጠው ለፍርድ
ከሐና ቀያፋ ከካህናቱ ደጅ
ከንሄሮድስ ዘንድ አቀረቡህ በአዋጅ
ግርፋት ህመሙ አልበቃ ብሎህ
በመስቀል ላይ ልትውል ተፈረደብህ
ሳዶር እና አላዶር ዳናት እና አይራ
ተፈልገው መጡ ለችንካር መከራ
አምስቱን ችንካሮች ቅንዋተ መስቀል
አይሁዶች አመጡ ገላህን ለማቁሰል
ሊያያዝ በችንካር እጅህ ተዘረጋ
የሰላም ባለቤት ደረትህ ተወጋ
ግፈኞቹ አይሁድ በአንተ ላይ ቀለዱ
ምራቅም ተፋብህ አንተኑ ሊጎዱ
ለእኛ ወገኖችህ ኃጢአት ላደከመን
የመስቀልህ ጥላ ማረፊያ ይሁንን

፯/7.ቸርነትህ ነው

ቸርነትህ ነው ያደረሰኝ እስከ ዛሬ
ቸርነትህ ነው የጠበቀኝ እስከ ዛሬ
ላመሰግንህ የእኔ ጌታ በዝማሬ/2×/
መክሊቴን ቀብሬ ባሳዝንህ
መብራቴንም ይዤ ባልጠብቅህ
በታላቅ ይቅርታ እንዳትረሳኝ
በፍቅርህ ጎብኝተህ ከሞት አውጣኝ
ከቤትህ ርቄ መኾ ጠገብኩኝ
በረሀብ እርዛት ተቸገርኩኝ
አምናለሁ አምላኬ እንድትምረን
ለይቅርታ መጣሁ ተቀበለኝ
አንዳች እንደሌለኝ አውቀዋለሁ
በአንተ ቸርነት ግን እመካለሁ
የከበደ ሸክሜ ይቀለኛል
ይቅርታ ለባሪያህ ይደርሰኛል
ከመቅደስህ ቆሜ ለመዘመር
ስራህን ለትውልድ ለመመስከር
እኔ ማነኝ ብዬ አስባለሁ
አምላክ ቸርነትህን አደንቃለሁ
በሰው እጅ መመካት አቁሜያለሁ
ረዳቴ አንተ ነህ አውቄያለሁ
አንተ ከጠበቅከኝ በህይወቴ
ቅጥሬ አይደፈርም መድኃኒቴ
የእኔን ስራ ተወው ምግባሬን
የመስቀሉን ነገር መርሳቴን

አዚሜን አንስተህ አንተን ልይህ
ኢየሱስ ክርስቶስ አምላኬ ነህ

፰/8.ምድረ ቀራንዮ

ምድረ ቀራንዮ ምድረ ጎልጎታ/2×/
መድኃኒት ክርስቶስ ባንቺ ተንገላታ/2×/
መስክሪ አንቺ ምድር ግፁዚቷ ስፍራ/2×/
መድኃኒት ክርስቶስ ያየብሽ መከራ/2×/
ደሙ እንደ ውሃ ሲፈስ በመስቀሉ ላይ/2×/
በቀራንዮ ቦታ መከራን ሲያይ/2×/
ፀሐይ ከለከለች ደማቅ ብርሃኗን/2×/
ለመሸፈን ብላ የአምላኳን እርቃን/2×/
ሁሉንም ለማድረግ ስልጣን ሲኖረዉ/2×/
በመስቀል ተሰቅሎ ፍቅሩን ገለፀው/2×/

በመስቀል ላይ ሆኖ ተጠማሁ እያለ/2×/
የእሾህ አክሊል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ/2×/
እጆቹ እና እግሮቹ በችንካር ተመተው/2×/
ይቅርታን ለመነ ለዚህ ኃጢአታቸው/2×/
ቸሩ መድኃኔዓለም እባክህ ማረን/2×/
ደካሞች ነንና እንዳንቀር ጠፍተን/2×/
በቆረስከው ሥጋ ባፈሰስከው ደም/2×/
አቤቱ ተራዳን እስከ ዘለዓለም/2×/

፱/9. ምክንያት ስላለኝ ነው

ምክንያት ስላለኝ ነው የምዘምርልሽ
ምክንያት ስላለኝ ነው ቅኔ የምቀኝልሽ
አሁንም ይብዛልኝ ፍቅርሽ(፪)
ከዚህ በላይ እንዳመሰግንሽ

አውቃለሁ ከደጅሽ ምን እንዳገኘሁኝ
አስታውሰዋለሁ ሸክሜን እንደጣልኩኝ
የለመንኩሽ ሁሉ መቼ ከንቱ ቀረ
ሰይጣን ተመለሰ እንዳቀረቀረ
ጠላት ቢከፋውም ለአንቺ በመቆሜ
አደገድጋለሁ ደግሜ ደግሜ

ልቤ አርፏል በአንቺ በእናቴ አማላጂ
እንቅፋት እሾሁ አይበቅልም በደጇ
በሚጣፍጥ ዜማ በኤፍሬም ውዳሴ

ሳሸበሸብልሽ ትረካለች ነፍሴ ጠላት
ቢከፋውም ለአንቺ በመቆሜ
አደገድጋለሁ ደግሜ ደግሜ

ውለታ ያለበት የማይከፈል
ሲመሽም ሲነጋም ያመሰግናል
ማርያም ማርያም ይላል ምድርና ሰማዩ
በልጅሽ መከራ አልፎለት ገዳዩ
ጠላት ቢከፋውም ለአንቺ በመቆሜ
አደገድጋለሁ ደግሜ ደግሜ

፲/10.አሰመ ለዓለም ምሕረቱ

አሰመ ለዓለም ምሕረቱ/2×/
አያልቅም ብዙ ነው የአምላክ ቸርነቱ/2×/
አመስግኑት ጌታን ሁላችሁ በአንድነት/2×/
መሐሪ ነውና ለሰው ልጆች ህይወት/2×/
የማይሞተው ሞቶ የተቀበረው /2×/
ከገሀነም እሳት እኛን ሊያድን ነው /2×/
ከማርያም የነሳው ያቅዱስ ስጋው /2×/
ቀራንዮ ሲውል የሚያሳዝን ነው/2×/
በፈጠረው ፍጥረት እጅግ ተሰቃይቶ/2×/
ነፍሳትን አወጣ ከሲኦል ለይቶ/2×/

፲፩/11.ተፈፀመ አለ

ተፈፀመ አለ ጌታ ነፍሱን ሰጠ
ስለእኔ ኃጢአት በመከራ አለፈ
በግፍ ተሰቃየ ፍዳን ተቀበለ
በጅራፍ ተገርፎ በእንጨት ተሰቀለ
ደፋ ቀና እያለ ሲወድቅ ሲነሳ
ያ ብርሃን ፊቱን በጥፊ ተመታ
በሀሰት ተከሶ በሀሰት ተገደለ
በውርደት ሸንጎ ፊት በአደባባይ ዋለ
በውሃ ጥም ዛለ በረሃብ ተቀጣ
ስለ ሰው ልጆች ሲል የሞት ፅዋን ጠጣ
አንቺ እለተ አርብ እንዴት ያለሽ በእውነት
ሰማያዊ አባት የተሰቀለብሽ
ከኋላ ከፊቱ በጠላት ተከቦ
ማንም አልነበረም የሚያፅናናው ከቶ
ሩህሩህ ጌታዬ ስለእኔ ብለህ ነው
ያን ሁሉ መከራ በትግስት ያለፍከው

፻፪/12.ያከብርዋ

ያከብርዋ ለሰንበት መላእክት በሰማያት ጻድቃን በውስተ ገነት/2×/
ወኩሉ ፍጥረት አሳት ወአናምርት እለ ውስተ ደይን ያእርፉ ባቲ እስመ ባቲ አእረፈ እም ኩሉ ግብሩ/2×/
ትርጉም፡-ያከብሯታል ሰንበትን መላእክት በሰማያት ጻድቃን በገነት/2×/
ፍጥረታት በሙሉ አሳዎችና አንበሬዎች በመቃብር ያሉ ያከብሯታል አምላክ በእርሷ አርፏልና ከስራው ሁሉ/2×/

፻፫/13.ኪዳነ ምሕረት

ኪዳነ ምሕረት እመቤት(2*)
ነይልን(2×)ካለንበት/2×/
ከሰማያት በላይ ካለው ከማደሪያሽ(2×)
ዝማሬ ከሞላው ከዘላለም ቤትሽ
የምድር ፍጥረታት ማርያም ማርያም ሲሉሽ(2×)
የቃል እናት እመቤቴ ነይ በሰረገላሽ/2×/
ከፀጥታ ወደብ ከፍቅር አውድማ(2×)
ከሰላሙ መንደር ከእውነት ከተማ
ሰአሊ ለነ ቅድስት ውዳሴሽ ሲሰማ(2×)
ከሚካኤል ከገብርኤል ጋር ነይልን ከራማ(2×)
ዘርፋፋው ቀሚስሽ ይውረድ ከሰማያት(2×)
እንባችን ይታበስ ባንቺ አማላጅነት
በፅዮን ዝማሬ ተሞላች ነፍሳችን(2×)
ንዒ(3×)እነበል እንደ አባቶቻችን(2×)
ፍጥረታት ሊድኑ ባማላጅነትሽ(2×)
የዘለዓለም ኪዳን አማኑኤል ሰጠሽ(2×)
ትውልድ ይህን አምኖ ብጽዕት ይልሻል(2×)
እናቴ መመኪያዬ ምርኩዜ ሆነሻል(2)
የልብን ሲያዋዩሽ ሰምተሽ ዝም አትዪም(2×)
ችግረኛን አይቶ ልብሽ አይጨክንም
ከወይን ጥቅሻ ፈጥነሽ ትደርሺለታለሽ(2×)
ከኃዘን ከመከራ ታሳርፊዋለሽ(2×)

፻፬/14.በርተሚዮስ ነኝ

በርተሚዮስ ነኝ አይነስውር ምስኪን
ከሩቅ የሰማሁት የጌታዬ ድምጹን
ከብዙ ሁካታ ጉርምርምታ መሐል
የክርስቶስ ድምፁ በግልጽ ይሰማኛል/2/

የልቦናዬ አይን ፈፅሞ ታውሯል
አይኔን ፈውስልኝ በርተሚዮስ ይላል
አብዝቼ እጮሃለው ጌታ ማረኝ ብዬ
በውስጤ እየታየኝ ሲምረኝ ጌታዬ/2/

አንተን አይሰማህም ይሉኛል ብዙወች
በሀጥያት ሰንሰለት ታስረህ አጥተክ ወርች
ስለዚህ አትልፋ ሲኦልን ጠብቃት
እንደዚ ቢሉኝም ጮሀለው ሳልታክት/2/

አዝ___

የከበበውን ሰው ገለል በሉ እያለ
በደሌን በደሙ ዋጋ እየከፈለ
ስለኔ የሞተው እየሱስ ይመጣል
የልቦናዬ አይን ገልጦ ያሳየኛል/2/

አዝ___

አብዝቼ ጮሀለው ጌታ ማረኝ ብዬ
በግልፅ እየታየኝ ሲምረኝ ጌታዬ
በውስጤ በደልስ ሂወቴ ዝላለች
በአምላኬ ቸርነት ሂወት ካላገኘች/2/

ፕሬ/15.አመቤቴ

አመቤቴ ጥላ ከለላዬ እረዳቴ የገነት ሙሽራ/2*/
የገነት ሙሽራ (3*) ማርያም የልዑል ማደሪያ/2*/

ፕሬ/16.በጌቴ ሴማኒ

በጌቴ ሴማኒ በአታክልቱ ቦታ/2×/
ለእኛ ሲል ጌታችን <u>በዓለም ተንገላታ</u>(2×)
አዳም እና ሔዋን ባጠፉት ጥፋት/2×/
በእኛም ደረሰብን <u>የዘለዓለም ሞት</u>(2×)
መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ/2×/
ይገርፉት ነበረ <u>ሁሉም በየተራ</u>(2×)
<u>ተጠማሁ</u>(3×)ሲላቸው/2×/
ኮምጣጤ አመጡለት <u>በሐሞት ቀላቅለው</u>(2×)
ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ/2×/
እያየች በመስቀል <u>ልጇ ሲንገላታ</u>(2×)
በአምላክነቱ ሳይፈርድባቸው/2×/
እንዲህ ሲል ጸለየ <u>አባት ሆይ ማራቸው</u>(2×)
በረቂቅ ስልጣኑ ሁሉን የፈጠረ/2×/
በሰዎች ተገርፎ <u>ሞተ ተቀበረ</u>(2×)

ፕሬ/17.አመቤታችን

አመቤታችን ማርያም ሀገራችንን/ኢትዮጵያን ጠብቂልን በምልጃሽ/2×/

ከመናፍቃን ከከሃድያን ከጠላት ሰይጣን ሰውረሽ እንድንሆን እርጂን የልጅሽ/በምልጃሽ/2×

፲፰/18.ከደመና በታች

ከደመና በታች እንዳይቀር ጸሎቴ(2×)/2×/
አሳርጊው(3×) ድንግል እመቤቴ/2×/

፲፱/19.አማን በአማን

አማን በአማን/2×/
አማኑኤል ተመስገን ለዚህ ፍቅርህ ምን ልክፈልህ/2×/
ድብቁን ኃጢአት አንተ ብትገልጠው
ይቅር ብለኸኝ ባትሸፋፍነው
እንደ ሰው በደል ብትቆጥር ጌታ
የእኔስ ኃጢአት የለውም ቦታ
በየደቂቃው ኃጢአት ሰሰራ
ስሰርቅ ስበድል አንተን ሳልፈራ
የእኔስ ኃጢአት ቢበዛ ምንም
በቁጣህ በትር አልገረፍከኝም
ምሕረትን ልከህ አድንን ዛሬ
ታውቆኛልና በኃጢአት መኖሬ
ዓለም በኃጢአት እየሳበቺኝ
በጽድቅ በደስታ መኖር አቃተኝ
የኃጢአት ጉዞ ጣፋጭ ቢመስልም
ውጤቱ መሮ ፍጹም አይጥምም
እንደ በደሌ ስላልከፈልከኝ
ተመስገን እንጂ ሌላ ምን አለኝ

፳/20.የአብርሃም አምላክ

የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም ቤዛ/2×/
ወገኖቹን ሁሉ በራሱ ደም ገዛ/2×/
የሐሰት ምስክር አቁመው ከሰሱት/2×/
በሞት እንዲቀጣ ሁሉም ፈረዱበት/2×/
ጲላጦስ ገረፈው በሰንሰለት አሰሮ/2×/
ከሮማዊው መንግስት እንዲኖር ተፋቅሮ/2×/
ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ/2×/
እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ/2×/
በብርሃን ዙፋን ላይ የቆሙት እግሮቹ/2×/
በችንካር ላይ ሆነው ምንም አልሰለቹ/2×/
የብርሃን አክሊልን ለስማዕት ያደለ/2×/
የእሾህ አክሊል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ/2×/

፸፩/21.እስመ ለዓለም ምሕረቱ

እስመ ለዓለም ምሕረቱ/2×/
አያልቅም ብዙ ነው የአምላክ ቸርነቱ/2×/
አመስግኑት ጌታን ሁላችሁ በአንድነት/2×/
መሐሪ ነውና ለሰው ልጆች ህይወት/2×/
የማይሞተው ሞቶ የተቀበረው /2×/
ከገሀነም እሳት እኛን ሊያድን ነው /2×/
ከማርያም የነሳው ያቅዱስ ስጋው /2×/
ቀራንዮ ሲውል የሚያሳዝን ነው/2×/
በፈጠረው ፍጥረት እጅግ ተሰቃይቶ/2×/
ነፍሳትን አወጣ ከሲኦል ለይቶ/2×/

፸፪/22.ባክኛለሁና

ባክኛለሁና በሥጋ ፈተና
የዚህ ዓለም ሀዘን ጫፍ የለውምና
ፈጥነሽ ወደ እኔ ነይ ከትንሿ ቤቴ
አጽናኚኝ እመ አምላክ ድንግል እመቤቴ
ባህሩ ትልቅ ነው ድንግል እመቤቴ
ትንሽ ናት መርከቤ ድንግል እመቤቴ/2×/
የመንገዴ መሪ ድንግል እመቤቴ
አንቺ ነሽ ወደቤ ድንግል እመቤቴ/2×/
በመንገዴ ብዝበል ድንግል እመቤቴ
ዓለም ትስቃለች ድንግል እመቤቴ/2×/
መመኪያ እመቤቴ/ታ ድንግል እመቤቴ
ወደ የት ናት እያለች ድንግል እመቤቴ/2×/
በቀቢጸ ተስፋ ድንግል እመቤቴ
እንዳልወድቅብሽ ድንግል እመቤቴ/2×/
በቀንም በሌሊት ድንግል እመቤቴ
ተስፋዬ አንቺ ነሽ ድንግል እመቤቴ/2×/
የለም ያተረፍኩት ድንግል እመቤቴ
ወጥቼ ወርጄ ድንግል እመቤቴ/2×/
ትርፌ አንቺ ብቻ ነሽ ድንግል እመቤቴ
ጽዮን አማላጄ ድንግል እመቤቴ/2×/

፸፫/23.ስምሽን ጠርቼ

ስምሽን ጠርቼ መቼ አፍራለሁ
ማርያም ብዬ መች እወድቃለሁ
የምጽናናበት ስምሽ ነውና
ድንግል ሆይ ላቅርብ ለአንቺ ምስጋና
ጨለማ ውጦኝ በጠላት ሀገር
ለዘመናትም ስረገጥ ስኖር
ዲያቢሎስ ማርኮ ሲያሰቃየኝ

የዓለሙን መድኅን ወለድሽልኝ
ከአባቶቼ ርስት ከሀገር ወጥቼ
በአህዛብ ሀገር ስኖር ሸሽቼ
ደርሰሽ አጽናንተሽ አከበርሺኝ
ብቸኝነቴን አስረሳሺኝ
ድንኳኑ ሞልቶ ሰዉ ታድሞ
አስተናባሪው በጭንቀት ቆሞ
ምን አቀርባለሁ ብዬ ስቸገር
ምልጃሽ ደርሶልኝ ዳንኩኝ ከማፈር
ያሰብኩት ሀሳብ ደመና ሆኖ
ቢበተንብኝ እንደ ጉም ተኖ
ይሆናል ያልኩት ሳይሆን ቢቀር
በእመ አምላክ እኔ መቼም አላፍር
እናት አባቴ ባያስታውሱኝ
ይህች ዓለም ንቃ ገፍታ ብትተወኝ
አንቺ ካለሽኝ ምን እሆናለሁ
አውሎ ነፋሱን ባህሩን አልፋለሁ
ጠላቴ ደርሶ ቢያንገላታኝ
መከራ አብዝቶ ቢያስጨንቀኝ
አላቋርጥም የአንቺን ምስጋና
ውለታሽ ድንግል አለብኝና
ክፉዎች ደርሰው ቢዝቱብኝ
አንቺን መውደዴን አያስተዉኝ
በአህዛብ መሐል ስምሽን ስጠራ
መከታ ሁኚኝ እናቴ አደራ
ከአባቶቼ ርስት ከሀገር ወጥቼ
በአህዛብ ሀገር ስኖር ሸሽቼ
ደርሰሽ አጽናንተሽ አከበርሺኝ
ብቸኝነቴን አስረሳሺኝ

ሿ፱/24.እመቤቴ የአምላክ እናት

እመቤቴ የአምላክ እናት
ላመስግንሽ ቀን ከሌሊት
ለልጅሽም ክብር ውዳሴ
ታቀርባለች ዘወትር ነፍሴ/2×/
ልቤ ተነሳሳ ተቀኘ ለክብርሽ
በፍጹም ትህትና ሊያመሰግንሽ
ጽዮን መጠጊያ ነሽ የአብርሃም ድንኳን
የታጠረች ተክል እመ ብዙኃን
የለመለመች መስክ አምላክ የመረጣት
የጽላቱ ኪዳን ታቦቱ ድንግል ናት
የሰማይ የምድር ንግሥት ናትና
ክብር ይገባታል ዘወትር ጠዋት ማታ
አደራሽን ማርያም የሁሉ እናት

በምልጃሽ አስቢኝ ኋላ ስራቆት
ያንን የእሳት ባህር አሻግሪኝ ድንግል ሆይ
እንዳልወድቅ እንዳልሞት ከቶ እንዳላይ ስቃይ

፳፭/25.መዘንጋት በአለበት

መዘንጋት በአለበት በታናሽ ህሊና
መዘመር ልጀምር ለድንግል ምስጋና
እኔስ በውዳሴሽ ባሕር እዋኛለሁ
ገናንነትሽን ክብርሽን እያሰብኩ

የትህትናሽ ነገር ቢወሳ አያልቅም
ታነቢያለሽ እና ለዚህ ክፉ ዓለም
ድንግል ሆይ ለኃጥአን ታስቢያለሽና
ልቦናዬ በአንቺ በምልጃሽ ተፅናና

ማርያም ሆይ ስለዚህ እንወድሻለን
አንቺን ተማጽነናል እንድታማልጂን
ዘወትር እጆችሽ ተዘርግተዋልና
ስለ በደለኞች ሊያቀርቡ ልመና

እሳታውያኑ ሱራፌል ኪሩቤል
ለነኩት የአልቻሉት የእሳቱን ነበልባል
አንቺ ግን ታቀፍሽው ሳምሽው በክንፈርሽ
ከፍጥረት ለይቶ ፍፁም ስላፀናሽ

ማርያም ሆይ ስለዚህ እንወድሻለን
አንቺን ተማጽነናል እንድታማልጂን
ዘወትር እጆችሽ ተዘርግተዋልና
ስለ በደለኞች ሊያቀርቡ ልመና

፳፮/26.ድንግል የዚያን ጊዜ

ድንግል *የዚያን ጊዜ*/2/ ሐዘንሽ በረታ /2/
በመስቀል ላይ ሆኖ ልጅሽ ሲንገለታ /2/

የግፍ ግፍ ደርሶበት የዛን ጊዜ ተጠማሁ ሲልሽ
ለውሻ ያጠጣሽ በወርቅ ጫማሽ /2/

ሴቶች ሲያባርሩት የዚያን ጊዜ እራርቶ ሆድሽ
ለፍጡር በማዘን ውኃ ያጠጣሽ /2/

ተጠማሁ እያለ የዚያን ጊዜ ሲናገር ልጅሽ

ታዲያ እንደምን ቻለ ወላድ አንጀትሽ/2/

እንደዚያ ስታለቅሽ የዚያን ጊዜ ሐዘን ሲውጥሽ
እነማን ነበሩ ያስተዛዘኑሽ /2/

ስታለቅሽ በማየት የዚያን ጊዜ እራርቶ ልጅሽ
ዮሐንስን አጽናኝ እንደልጅ ሰጠሽ/2/

፳፯/27. እኔስ በምግባሬ

እኔስ በምግባሬ ደካማ ሁኛለሁ (2)
እዘኝልኝ ድንግል እለምንሻለሁ (2)

ያንን የእሳት ባሕር እንዳላይ አደራ
ድረሽልኝ ድንግል ስምሽን ስጠራ (2

የዳዊት መሰንቆ የኤልያስ መና
የናሆም መድሃኒት ንዒበደመና (2)

አንቺ ነሽ ጉልበቴ በደከመኝ ጊዜ
የልቤ መጽናኛ እረዳት ምርኩዜ (2)

አፈሳለሁ እምባ በጣም ተጨንቄ
እማጸንሻለሁ በደሌን አውቄ (2)

፳፰/28.ጌታዬ ሆነ ደም ግባት አልባ

<u>ጌታዬ ሆነ ደም ግባት አልባ፣</u>
<u>ጀርባዉ በጅራፍ ስለእኔ ደማ፣</u>
<u>የእኔን መገረፍ እርሱ ተገርፎ፣</u>
<u>ክብር አለበሰኝ እርሱ ተገፎ፣ (×፪)</u>

በሀሰት ሸንጎ ወጥመድ ተጠምዶ
ጌታ ተያዘ ሕይወቴን ፈቅዶ
ክፋዎች ቢያዩት እንደ ወንበዴ
ለእኔ ግን ሆኗል መውጫ መንገዴ (×፪)
ታስረሃል ስለእኔ ኢየሱስ መድኅኔ
ታስረኃል ስለኔ ኢየሱስ መድኅኔ
<u>አገቱኒ ከለባት ብዙኀን</u>
<u>ወአኀዙኒ ማኅበሮሙ ለእኩያን</u>
<u>አገቱኒ ከለባት ብዙኀን</u>

ሲዘብቱበት ምራቅ ሲተፉ
የማይደፈር ደፍረው ሲዘልፉ
በከበቡት ፊት ቃል ከለከለ
እኔ እንድናገር እርሱ ዝም አለ (×፪)
ታርደሃል ስለእኔ ኢየሱስ መድኅኔ
ታርደሃል ስለእኔ ኢየሱስ መድኅኔ
ቀነጢኒ እደውየ ወእገርየ
ወጎሎቁ ኩሎ አዕጽምትየ
ቀነጢኒ እደውየ ወእገርየ

ሕይወት መንጭቷል ተወግቶ ጎኑ
ለከሳሾቹ ተርፏል ማዳኑ
እጅ እግሩን ሚስማር ሲቸነክርው
የሞትን እሾህ ከኔ ነቀለው (×፪)
ተወጋ ስለእኔ ኢየሱስ መድኅኔ
ተወጋ ስለእኔ ኢየሱስ መድኅኔ
ወወደዩ ሐሞተ ውስተ መብልዕየ
ወአስተዩኒ ብሒዓ ለጽምዕየ
ወወደዩ ሐሞተ ውስተ መብልዕየ

እርቃኑን ሆኖ ፈተለው ልብሴን
አንዲሁ ወዶኝ ጠጣ ኾምጣጤ
በምሕረቱ ጠል ነፍሴን አርከቶ
አለመለመኝ እርሱ ተጠምቶ (×፪)
ተጠማ ስለእኔ ኢየሱስ መድኅኔ
ተጠማ ስለእኔ ኢየሱስ መድኅኔ

፳፱/29.እጠበኝ ቆሸሻለሁ

እጠበኝ ቆሸሻለሁ አምላኬ በድያለሁ
ያለ እናት ያሳደከኝ ያለ አባት የጠበከኝ
ያን ሁሉ ዛሬ ረሳሁ እጠበኝ ቆሸሻለሁ

ከድንኳኑ ብታስገባኝ ሞገስ ስጥተህ
የአፍኒንን ምግባር ይዤ አስቀየምኩህ
ቅብዓ ሜሮን ያተምክበት ልጅነቴ
እንዳይጎድፍ ጠብቅልኝ ቸር አባቴ

ኃይል አኑረህ እንደ ሶምሶን በፀጉሬ
ጎልያድን አስጥለክኝ በጠጠሬ
አቅም ቢያንስኝ ለሥጋ ጦር ተሸንፌ

ደጅህ መጣሁ የዕንባ መባ በአይኔ አቅፌ

እንዳትረሳኝ በመዳፍህ ቀርፀኸኛል
እንዳተወኝ ያለመጠን ወደኸኛል
ባትሰነዝር ልትቀጣኝ በሞት በትር
የትግስትህ ሰሌዳ ነው የኔ ክብር

በከንፈሬ ጥበብ ፅፌ ቅኔ ቢፈስ
በመታበይ አሳዘንኩት ያንተን መንፈስ
ፍቅር ሰተህ በእቅፍህ ስር ያሳደከኝ
እባክህን በበደሌ አትቅሰፈኝ

፴/30.ሞገድ ሲመታኝ ማዕበሉ

ሞገድ ሲመታኝ ማዕበሉ

ማን ያድነዋል ሁሉም ሲሉ
በሰላም አለፍኩ በፀጥታ
ሁሉ ተችሎ ለአንተ ጌታ(፪×)

በአንተስ ቁስል ተፈወስኩኝ
ጌታ በፍቅር ተማረኩኝ
ሞቴን ሽረኸው በአንተ ሞት
ይኸው አቆምከኝ በህይወት(፪×)

ደጅ ስጠና ስማፀንህ
መቼ ጨከነ ጌታ ልብህ
እንደ ቀራጩ አጎነበስኩ
ምህረት ፀጋህን ከእጅህ ለበስኩ(፪×)

ዘወትር እልል ብል ብዘምር
ስለገባኝ ነው የአንተ ፍቅር
ጌታ ብጠራው ስምህን
ለውጠኸው ነው ታሪኬን(፪×)

አይኖቼ አያየም ካንተ በቀር
የምትወደድ የምትፈቀር
ዘመድ ወገኔ ሆነኸኛል
እኔን የሚችል የት ይገኛል (፪×)

፴፩/31.ማረኝ መመኪያዬ

ማረኝ ማረኝ ማረኝ መመኪያዬ፣
አርጅቻለሁና በኃጢአት ጎስቁዬ።(×2)

ከፊቴ ናትና ኃጢአቴ ሁል ጊዜ፣
ተውጫለሁ እኔስ በሃዘን በትካዜ፣(×2)
በፊትህ ክፋትን አድርጌአለሁ እኔ፣
ምንም ጽድቅ አልሠራው በሕይወት ዘመኔ።(×2)

ከፊትህ መቅበዝበዝ መሰደድ ፈለኩኝ፣
ኃጢአት ከኋላዬ እያሳደደችኝ፣(×2)
ወዴት አሄዳለሁ መሸሸጊያም የለኝ
ምሕረት መጠጊያ ዋሻ ካልሆነችኝ።(×2)

የተሰባበረው አጥንቴ እንዲጠገን፣
በምሕረት እና በቸርነት ዳስሰኝ፣(×2)
የቀና መንፈስን አድስ በልቤ ውስጥ፣
ነፍሴ በእሺታ በተስፋ ትለወጥ።(×2)

ቅዱስ መንፈስህን ከእኔ ላይ አትውሰድ፣
በንስሐ ድኜ በተስፋ እንድላመድ፣
አቤቱ ንጹሕ ልብ ፍጠርልኝና፣
በደስታ ልስከር በፍቅርህ ልጽናና።(×2)

ዝፈ/32..አልተወኝም

አልተወኝም ጌታ ለካስ ይወደኛል/2x
ዛሬም ስበድለው ልጄ ነኽ ይለኛል/2*/
በበደል ጉራንጉር በኃጢአት ጫካ
ብጠፋበት እንኳን አልተወኝም ለካ
ዛሬም ልጄ ብሎ ዳግም ይጠራኛል
ለካስ አልጠላኝም ጌታ ይወደኛል
አዝ....
ለሥልጣን ለክብሬ ብዬ ስከዳው
ለገንዘብ አድልቼ እኔ ስረሳው
ለእኔ ያለው ፍቅር አልቀነሰብኝም
ዛሬም ይወደኛል ጌታ አልጠላኝም
አዝ....
ታዲያ ለዚህ ፍቅሩ ለሌለው ወሰን
ከጭንጫ መቃብር ላወጣኝ እኔን
በሕይወቴ ኹሉ ፍጹም ለመራኝ
ክብር እና ምስጋና አቀርባለሁኝ

፴፫/33. ስምህ በሁሉ

ስምህ በሁሉ ተመስገነ
ከክብር በላይ ክብርህ ገነነ
አንተን ማወደስ ያስደስተናል
ስምህን ማክበር ክብራችን ሆኗል(፪)

አምላክ ተመስገን በሰማያት
ስምህ ይወደስ በፍጥረታት
ከህፃናት አፍ ምስጋና ይውጣ
አንተን ማመስገን ይሁን የኛ ዕጣ(፪)

በምግብ እጦት ብንሰቃይም
ማህሌትህን አናቋርጥም
የመከራ ዶፍ ቢወርድብንም
እንዘምራለን ለአምላካችን ስም(፪)

ሰማዩ ዝናብ ደመና ቢያጣም
ፍቅርህ በእኛ ውስጥ አላቋረጠም
ቸርነትህን እንጠብቃለን
ከአንተ ደጅ ጌታ የት እንሄዳለን(፪)

፴፬/34.ነፍሴ ሆይ

ነፍሴ ሆይ/ቮ/እግዚአብሔርን ባርኪ
ነፍሴ ሆይ/ቮ/እግዚአብሔርን ባርኪ
አጥንቶቼም ሁሉ/ቮ/የተቀደሰ ስሙ

በደስታ ዘምሪ በአዲስ ምስጋና
ጸጥታ እና ሠላም አድኖሻልና
መሰንቆውን አንሺ ቅኔ ተቀኚለት
ለውጦሻል እና በደስታ ዘፍት

ሀሴትን አድርጊ ነፍሴ በእግዚአብሔር
ይሰጥሻልና በክብር ላይ ክብር
ደሴቶች ሲያወሩ በየስታ መንፈስ
እየተወያዩ ስለ ሥሉስ ቅዱስ

ሠማያት ሚያወሩ ጽድቅን ሲወያዩ
ሚጠራው አድምጪ ቀላዩን ቀላዩ
ደመናው ጭጋጉ በዙሪያው ከበዉት
ቅኔ ያቀርባሉ ለፍጥረታት አባት

መብረቅም ይሠማል ሠማዩን ሠንጥቆ
ምስጋናውን ሊያቀርብ ጊዜውን ጠብቆ
በፊቱ ይነዳል እሳትም በግርማ
ምድር ተናወጠች ነጎድጓዱን ሠምታ

፫፭/35. እውነት ስለሆነ

እውነት ስለሆነ እየሱስ ክርስቶስ
ዋለ ባደባባይ ሲሰደብ ሲከሰስ
የሃሰት ዳኝነት አምላክን ወቀሰው
ህይወት ሰጠን እንጂ ጥፋቱ ምንድነው/፪/

ከቃሉ እምነት ባያገኙበትም
ዝምታውን አይተው አላዘኑለትም
ባላወቁት መጠን ጠሉት ካለበደል
ጥፋቱ ምን ይሆን የሚያደርስ እስከመስቀል /፪/

የልቡን ትህትና ፍቅሩን ሳያስተውሉ
ቸሩ ጌታችንን አቻኩለው ሰቀሉ
እሩሁን ጌታ ቸንክረው ሰቀሉት
ሞትን አስወግዶ ቢሰጣቸው ህይወት /፪/

ስለ ቸርነቱ ስድብን ከፈሉት
ስለ እርህራሄው የሾህ አክሊል ሰጡት
ሀሞት እና ከርቤ ኮምጣጤ ደባልቀው
መራራ አስጎነጩት ጨክኖ ልባቸው /፪/

ፈውስን ለሰጣቸው ልባቸውን ሞልተው
አሉት ወንበዴ ነው ስቀለው ስቀለው
ከጁ በረከትን የተሻሙ ሁሉ
ይጮሁ ነበረ ይገደል እያሉ /፪/

፴፮/36.የጴጥሮስን እንባ

የጴጥሮስን እንባ ስጠኝ እልሀለው

ሀጢአቴን ልናዘዝ ፍቅርህን እያሰብኩ
በሞት ጥላ ውስጥ እንኳን ብሄድ ጌታ ሆይ/2/
ልቤን በፍቅር ውሃ አጠበው እባክህን

ቸርነትህ በዝቶ ምህረት ቢያሰጠኝ
እጆቼን ዘርግቼ እማጸናለውኝ
ደምህ የፈሰሰው ለኔ ስለሆነ/2/
በሀጢአት ልትተወኝ ልብህ አልወሰነ

አለማዊ ምግባር ልቤ ቢከተልም
ከዚህ ሁሉ ማዳን ጌታ አይሳንህም
ሀጢአት እየሰራው ባስቀይምህም/2/
በሂሶጵ እርጨኝ ጌታ አንጻኝ እባክህ

ዳቢሎስ ያመጣው ጸጸት የውድቀት ነው
የይሁዳ ምሬት መሞት ነው ፍፃሜው
ይህንን መማረር እኔ አልፈልግም/2/
የውድቀት ጉዞ እንጂ ፍፃሜ የለውም

ጴጥሮስ አባብሎ የተማጸነበት
ፍቅሩን በንስሀ ስቦ ያመጣበት
ፍፃሜው የሚያምር ንስሀ ስጠኝ/2/
የለቅሶ አምሀ የእንባ ሕይወት ስጠኝ

፴፯/37.በምድራዊ ህይወት

በምድራዊ ህይወት(2×) በፈተና ቦታ/2×/
ማርያም ትጠብቀን እጆቿን ዘርግታ ድንግል ትጠብቀን እጆቿን ዘርግታ(2×)/2×/

፴፰/38.ከክርስቶስ ፍቅር

ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማነው/2×/
መከራ ችግር ስቃይ ወይስ መራቆት ነው/4×/
አንፈራም አንሰጋም አንጠራጠርም/2×/
እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ ይኖራል ለዘለዓለም/4×/
የሰማይ ቤታችን አማኑኤል የሰራው/2×/
ግንቡ ንጹሕ ውሃ መሰረቱ ደም ነው(2×)መሰረቱ ደም ነው/2×/
ሳይነጋ ተራምደን እንግባ በጠዋት/2×/
በደሙ መስርቶ ከሰራልን ቤት(2×) ከሰራልን ቤት/2×/
ከቶ የት ይገኛል እንዲህ ያለ ቤት/2×/
የውሃ ግድግዳ የደም መሰረት(2×) የደም መሰረት/2×/
የውሃ ግድግዳ የደም መሰረት/2×/
ይኸው እዚህ አለ የአማኑኤል ቤት
ይኸው እዚህ አለ የሥላሴ ቤት(2×)

፴፱/39.ያዕቆብ ከቤርሳቤህ

ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ወደ ካራን ሲሄድ
የለውም ነበረ አማካሪ ዘመድ
ፀሐይ ጠልቃ ነበር ከዚያ እንደደረሰ
ከእራሱም በታች ድንጋይ ተንተራሰ
ህልምንም አለመ ታላቁን ራዕይ
መሰላል ተተክሎ ከምድር እስከ ሰማይ
ሲወጡ ሲወርዱ መላእክት በእርሷ ላይ
እግዚአብሔርም ቆሞ ከላይ ከጫፏ ላይ
የአባቶችህ አምላክ እኔ እግዚአብሔር ነኝ
ይህንን ምድር ለርስትህ እሰጥሃለሁኝ
ዘርህ እንደ አሸዋ በምድር ይበዛል
በአራቱም ማዕዘን ህዝብህም ይሆናል
አበው በምሳሌ እንደተናገሩት
ከምድር እስከ ሰማይ አምላክ የዘረጋት
በላይዋ ተቀምጦ በግልጽ የታየባት
የያዕቆብ ራዕይ እመቤታችን ናት
ሰማይና ምድር የሚታረቁባት
ወልደ እጓለእመህያው የተወለደባት
መላእክት በሰማይ በአንድ የዘመሩላት
ታላቂ መሰላል እምቤታችን ናት

፵/40.ኃይሌም ዝማሬዬም

ኃይሌም ዝማሬዬም እርሱ ነው ዘላለም
ከብሮ ያስከበረኝ እንደ እግዚአብሔር የለም
እንደ እግዚአብሔር የለም ክብር ለሱ ይሁን
ታላቅ ነው ዘላለም

አቤቱ ጉልበቴ ሆይ አቤቱ መጽናናቴ
ታትመህል በውስጤ ተስለህል ከፊቴ
አያውህ አሻግሬ በተራሮች ከፍታ
ጨለማየን ስትገፈው ሰንሰለቴን ስትፈታ

ዶኪሜ ነህ ኢየሱስ ዶኪሜ ነህ ጌታየ
እግሮቼ ላይ ይፈሳል የማይቆመው እንባየ
ናፈቀችህ መንፈሴ እንደ ዋላ ተጠማሁ
ስምህን አውጀበት ይሸበራል ከተማው

ዲዳው አፉን ከፈተ ምርኮኛው ነጻ ወጣ
ምድር ባንተ አረፈች ለተገፉት ቀን ወጣ
የእንባየ ምትክ ሆኖ ጽድቅህ መንደሬን መላ
የረዳኝ የሚረዳኝ ማን አለ ካንተ ሌላ

አቁሞኛል ግሳፄህ አቁሞኛል ፍቅርህ
ወዳጅ አበዛህልኝ ወዳጄ እያልኩህ
ጸጋ ሞልቶ ፈሰሰ የዝማሬ ማእበል
ደጅህ በመንጋ ሞላ ጌታየ ሆይ ምን ልበል

ቫጂ/41.አጋጣሚ አይደለም

አጋጣሚ አይደለም መትረፊ መዳኔ
የጌታ ታምር ነዉ ኧረ ይገርማል የኔ
ሞት እንቅልፍ ሆነልኝ ጭንቀቴ ቀለለ
የረዳኝ ጌታ ነዉ ዉደ የተከተለ

ማነዉ በዚያ በረሃ
ያበላኝ መና ያጠጣኝ ዉሃ
ማነዉ የደገፈኝ
ጥልቁን ሸለቆ ያሻገረኝ
አንተነህ ለኔ እናት አባቴ
ፍጹም ወዳጄ ስጋና አጥቴ
አይኔ አይነቀል ከዙፍንህ
ፊት አያዞርም ፍቅር አይንህ

አዝ=====

ወሮኝ ድቅድቅ ጨለማ
ተስፋዬ ደክሞ ልቤ ሲደማ
አይቶ ሲፈስ እባዬ
ዳመና ጠቅሶ መጣ ጌታዬ
ጸሀይ ነዉና የብርሀን አምዴ
ኢየሱስ ለኔ ሕይወት መንገዴ
አልተሸነፍኩም ዉደ አግዞኛል
መቃብር ደፍኖ ሕይወት ሰቶኛል

አዝ======

ሲለይ ነፍስ ከስጋ
በጨለማ እንቅልፍ በክፉ አደጋ
ዳንኩኝ ሞት እያየኝ
የንስሀ እድሜ ጨመረልኝ
በጽድቁ አይደለም የተረፍኩት
በርሱ ፍቅር ነዉ በርሱ ምህረት

ብቻዬን ሆኝ ሁሌ ማለቅሰዉ
እየበደልሁት ስላዳነኝ ነዉ

አዝ====

ሞት ሆይ መዉጊያህ የታለ
ሁሉም ጥሎህል እየታገለ
ሶኦል ድኗል ሀጥንህ
ባዶ ቀርተሃል ተበዝብዘሀ
በራሱ መንግስት ፈጥሮ ባለማ
የልጁን ህይወት ማንም አይቀማ
መቃብር ያልፍል ባገልግሎቴ
ተከፍቶልኛል ደጁ ያባቴ

ቫፀ/42.በንፁህ ደሙ

በንፁህ ደሙ ያዳነን
ከወደቅንበት ያነሳን
ብዙ ነው የእርሱ ውለታ
እንዘምራለን ለጌታ

አዝ

ቀና ብለናል በክብር
አንገቱን ደፍቶ በፍቅር
ስለ እኛ ብዙ ሆነልን
የብርሀን አክሊል ደፋን
(የዓለም መድኃኒት ጌታ ነው
ጠላታችንን ያሰረው)x2

አዝ

እርቃኑን ሆኖ ሸለመን
እየደከመ አቆመን
እርሱ በመስቀል ሲሞት
እኛ ተግፍን በሕይወት
(የዓለም መድኃኒት ጌታ ነው
ጠላታችንን ያሰረው)x2

አዝ

እስከ ሺህ ትውልድ ይምራል
ፍቅር ነውና ይራራል
አይዝልም የእርሱ ትከሻ
መጨረሻ ነው መድረሻ
(የዓለም መድኃኒት ጌታ ነው
ጠላታችንን ያሰረው)x2

አዝ

በደም ያጌጠ ልብስ አለን

ከአማልክት ማንም አይመስለው
ትውልዱ ማዳኑን ይስማ
ነግሷል በፅዮን ከተማ
(የዓለም መድኃኒት ጌታ ነው
ጠላታችንን ያሰረው)x2

ቁ፫/43..ሀይሌ ብርታቴ

ሀይሌ ብርታቴ ክብሬ ሞገሴ(2)
የዘላለሙ የአብርሃሙ ሥላሴ (2)

ተመረጠች ነፍሴ አንተን ለማወደስ
ከላይ ከአርያም ከሥላሴ መቅደስ
በአንድነት ሦስትነት በዙፋኑ ሞልቶ
የሚሳነው የለም ለሥላሴ ከቶ
አዝ.....

ከመንገድ ዳር ልቁም የወደቀ ላንሳ
የተራበን ላብላ የታመመ አልርሳ
እንደ አብርሃም አድርገኝ እንደ ደጉ አባት
ቤቴ እንዲሞላ በአንተ በረከት

አዝ.....

ጠፈሩን በውሃ በጥበብ የሰራ
እኔስ ይገርመኛል የሥላሴ ስራ
ኑ እና ተመልከቱ ተአምራት ሲሰራ
ሰዎች እልል በሉ ወላድ ሆነች ሣራ

አዝ.....

አብ አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ወዶናል
ወልድ በተዋህዶ እኛኑ መስሎናል
ሀይሉ ተገለጠ የመንፈስ ቅዱስ
በቅዱሳን አድሮ ሲያድን ሲፈውስ

ቁ፬/44.እንደ ምህረት ብዛት

እንደምህረትህ ብዛት ማረኝ መተላለፌን ደምስስልኝ

አንተን ብቻ በደልኩኝ ትዛዝህን ተላለፍኩኝ

አዝ.....

እጅግ በዛ የኔ ሀጥያት ከፀጉሬ

በመቅደስህ እጮኻለሁ አቀርቅሬ

አትቅሰፈኝ በመአትህ አትገስፀኝ

ጌታዬ ሆይ የማዳንህን ደስታ ስጠኝኝ

አዝ.....

እንደማውቅህ በአደባባይ ምን ብናገር

ስራዬ ግን ይህን ነገር አይመሰክር

ከእልፍኝህ ብሄድ እርቄ ከአንተ ፍቅር

ሁሉን ከሰርኩ አላተረፍኩ አንዳች ነገር

አዝ.....

ማን እንደኔ ከተውልዱ የበደለ

መሐሪ አምላክ ከአንተ በቀር ወዴትአለ

የዳዊት ልጅ ማረኝ ብዬ እጮሃለሁ

እያነባሁ በጉልበቴ እሰግዳለሁ

አዝ.....

በመዳፈር እንደ አፍኒን እንደፊንሀስ

ሰውነቴን አቆሸሽኩኝ ያንተን መቅደስ

አሳልፈህ እንዳትሰጠን ለሀጥያቴ

እንደቀድሞ ልጄ በለኝደጉ አባቴ

ምን አለ ያንደልክብኝ

ሳትነፍገኝ ሁሉን ሰተኸኝ

ሆነኸኝ እናት እና አባት

አለፉ ብዙ ዘመናት (2)

አዝ

አኖርከኝ ዛሬም በጤና

ወጥቼ ገባሁ በደና

መንገዴን ሰጥቼሀለው

ስትመራኝ እከተላለው

አዝ

ወረት አታውቅም ጌታዬ

መች ቀረ ፈሶ እንባዬ

ህይወቴ በመዳፍህ ነው

መፍራቴ ከቶ ለምን ነው

አዝ

አውቀኸኝ ሳትሰራኝ ገና

ሞልተኸኝ ቅኔ ምስጋና

ካንተ ነው የተቀበልኩት

በመዝሙር የሰለጠንሁት

አዝ

መዛሌ በውሀ ጥም

በባዕድ ሀገር መድከም

በብዙ ስጋት ተጉዤ

ቁሜአለው ስምህን ይዤ

አዝ

በትዳር በልጅ ባርከኸኝ

የልቤን ደስታ ሰጠኸኝ

ስለያዝኩ ጌታ ያንተን እጅ

ተባልኩኝ የንጉሱ ልጅ

ቫጂ/45.እመቤቴ ማርያም

እመቤቴ ማርያም እለምንሻለው

በለቅሶ በዋይታ ፊትሽ ወድቄአለው

እመቤቴ ስሚኝ ተማጽኜሻለው /2/

እዝ

ሐዘኔን ጭንቀቴን ለማን እነግራለው

ችግሬን ጉዳቴን ለማን አዋያለው

እመቤቴ ስሚኝ ተማጽኜሻለው /2/

አዝ

ሐዘኑ በዛብኝ መከራው ከበደኝ

እንደምን ልቻለው እኔስ ብቻዬን ነኝ

የአማኑኤል እናት ፈጥነሽ ድረሽልኝ /2/

አዝ

በጣም ተንገዳገድኩ ልወድቅ ነው እኔ

እመ አምላክ ደግፊኝ ቁሚልኝ ከጎኔ

ምንም አጋር የለኝ ከአንቺ በቀር ለእኔ /2/

ቫኜ/46.አቤቱ ደግ ሰው

አቤቱ ደግ ሰው አልቋልና/2/

ከምድርም ፍቅር ጠፍቷልና/2/

እንደ ቸርነትህ አድነን/2/

በደላችንን አትቁጠር/2/

አዝ

የረድኤት አምላክ ፍቅር ስጠን/2/

እንደ አሕዛቡ አታድርገን/2/

ክርስቲያን ነንና እንዋደድ/2/

እባክህ አንውጣ ካንተ መንገድ /2/

አዝ

አቤቱ ንጹህ ልብ ፍጠርልን/2/

ሰውን የሚያስወድድ ካለ እንከን/2/

እንደበታችንም እንዲናገር/2/

ስለ ሰላም ቋንቋ ስለ ፍቅር/2/

አዝ

በእግዚአብሔር ፍቃድ የሚመራ/2/

ከክፋት ደግነት የሚስራ/2/

አንደበቱ ሁሉ የታረመ/2/

ለቃለ ወንጌሉ የደከመ/2/

አዝ

ምግባርና እውነት የተሰጠው/2/

እባክህን ስጠን ሁነኛ ሰው/2/

አንተን የሚመስል በሕይወቱ/2/

ፍቅርና ትህትና የግል ሀብቱ/2/

አዝ

የማስመሰል ፍቅር እየበዛ/2/

ሰው እረክሷልና እንደዋዛ/2/

ፍጹም መዋደድን ስጠንና/2/

አዲስ ሰው እንሁን እንደገና/2/

አዝ

ደገኛ ሰው ማግኘት አስቸግሯል/2/

እስከመጨረሻው ማን ይጸናል/2/

ምግባሩ ትክክል እውነተኛ/2/

ልቡ የሚጸየፍ ከዳተኛ/2/

ቻኗ/47.ጊዜዬ እስኪደርስ

ጊዜዬ እስኪደርስ ወደ አንተ መምጫየ

ለንስሐ አብቃኝ አቤቱ ጌታየ /2/

አዝ

ብርሃኔ መድኃኒቴ ተስፋህ ይመልሰኝ

ጥፋቴን ደምስሰህ ይቅርታ አድርግልኝ

ተስፋዬ እረዳቴ አንተ አትጣለኝ

አምላኬ አታጥፋኝ ከሲኦል አድነኝ

አዝ

መኃሪ ይቅር ባይ ምሕረትህ ይጎብኘኝ

ከኃጢአት ፍላጻ ጸጋህ ይታደገኝ

አዳኜ መድሃኒቴ ሰላምን ላክልኝ

የዕድቅ ደጆችህን በፍቅር ክፈትልኝ

አዝ

አቤቱ ምህረትህ በእኔ ላይ ይሁን

ተጨነቅሁ አምላኬ ስጠኝ ሰላምን

ከክፉ እንድሸሽ አድነኝ እኔን

በጎ እንድሰራ ምራኝ መንገዱን

አዝ

ሕይወት ሞት ድኅነትን መኖራቸውን ባውቅም

ኃጢአት ውድቀት ጥፋት አያዘናጋኝም

ስርየት እንደማገኝ ተስፋ ቢኖረኝም

ትምክህቴ አንተ ነህ በሌላ አልመካም

አዝ

የበደሌ ብዛቱ የሚያስከፋም ቢሆን

በሥጋ በደምህ እጠብ ኃጢአቴን

ወደ አንተ እጮህለሁ አደራ ነፍሴን

በሰማያዊው ቤት አኑር ሕይወቴን

፵፯/47.ጌታ ሆይ

ጌታ ሆይ አይሁድ አማፅያን ሰቀሉህ ወይ

የዓለም መድኃኒት የዓለም ሲሳይ ሰቀሉህ ወይ/2×/

የአዳም በደል አደረሰህ አንተን ለመስቀል

የሐዋን ስህተት አበቃህ ለሞት ቸሩ አባት/2×/

ንጹህ ክርስቶስ ሆንክ ወንጀለኛ ብለህ ስለ እኛ

መስቀል አሸክመው አስረው ገረፋህ እያዳፋህ/2×/

ግብዞች እንደራሳቸው መስሏቸው

ምራቅ እየተፋ በፊትህ ቀለዱ አንተን ሊጎዱ/2×/

እጅና እግርህ በችንካር ተመታ የዓለም ጌታ

የእሾህ አክሊል ደፋህ ጎንህን ተወጋህ አልፋ ኦሜጋ/2*/

በመስቀል ላይ ተጠማሁ ስትል ታላቅ በደል

ሐሞትና ከርቤ ሰጡህ ቀላቅለው ጠጣ ብለው (2)

ይቅር ባይ ግልጽ በደላችን ሁሉን ሳታይ

አንተው ይቅር በለን በእኛ ሳትከፋ እንዳንጠፋ (2)

፵፰/48.የቀደመ በደላችንን

የቀደመ በደላችንን(2*) አታስብብን/2*/

አቤቱ ይቅርታ ፈጥኖ ይደረግልን አቤቱ ይቅርታ ፈጥኖ ይሁን ይደረግልን/2*/

፵፱/49. ምድረ ቀራንዮ

ምደረ ቀረንዮ ምደረ ጎልጎታ

መድኃኒት ክርስቶስ በአንቺ ተንገላታ/2/

መስክሪ አንቺ ምድር ግፁዚቷ ሥፍራ

መድኃኒት ክርስቶስ ያየብሽን መከራ/2/

ደሙ እንደውኃ ሲፈስ መስቀሉ 2/

በቀራንዮ ቦታ መከራውን ሲያይ/2/

ፀሐይ ከለከለች ደማቅ ብርሃኗን /2/

ለመሸፈን ብላ የአምላክን እርቃን/2/

በመስቀል ተሰቅሎ ፍቅሩን ገለጸው /2/

በመስቀል ላይ ሆኖ ተጠማሁ አያለ /2/

የሾህ አክሊል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ /2/

እጆቹን እግሮቹን በችንካር ተመተው/2/

ቸሩ መድኃኔዓም እባክህ ማረን/2//

ደካሞች ነንና እንዳንቀር ጠፍተን/2/

በቆረሰከው ስጋ ባፈሰሰከው ደም/2/

አቤቱ ተራዳ እስከ ዘላለም/2/

፱/50.ዝማሬ ዳዊትን

ዝማሬ ዳዊትን ተልዕኮ አርድዕትን ቅዳሴ መላእክትን/2×/
<u>የተቀበልክ አምላክ</u>(4×) የእኛንም ዝማሬ ተቀበል/2×/

የአፍሪካ ጤና ኮሌጅ ለገሀር ጊቢ ጉባዔ መዝሙር እና ሥነ ጥበብ ክፍል